# የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር የማማከር አገልግሎት ረቂቅ መመሪያ

## አጭር ማብራርያ (ሐተታ ዘምክንያት)

1. መግቢያ

በአለም አቀፍ ደረጃ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የማማከር አገልግሎት መስጠት የጀመሩት ረጅም አመታት ያስቆጠረ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም በሀገራችን ያለው የማማከር አገልግሎት ትኩረት ተሰጥቶት ስርአት ተዘርግቶ እየተተገበረ አይደለም። የትስስር አካላት በጋራ የሚሰሩበት የተቀናጀ የህግ ማእቀፍ ባለመኖሩ ምክንያት የማማከር አገልግሎት  ውጤታማ፣ አሳታፊ እና አካታች አለመሆን፣ እንዲሁም የሀብት ብክነት ማስከተሉ ዋነኛ ችግሮች ናቸው።

በመሆኑም የትስስር አካላትን በማሳተፍ የማማከር አገልግሎት ስራን መተግበር ችግሩን ለመፍታት ቁልፍ ሚና እንዳለው ይታመናል። ይህ መመሪያ በከፍተኛ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪ ውስጥ የሚደረግ የማማከር አገልግሎት የኢንዱስትሪውን ችግር መሰረት ያደረገ እና የኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነት የሚያሳድግ፣ የትስስር አካላት መካካል ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል በማስፈን ገቢያቸውን የሚያሳድጉበት፣ በማማከር አገልግሎት የሚሳተፉ አካላት የተለያየ ማበረታቻ የሚያገኙበት እና ክህሎት የሚያሳድጉበት እንዲሁም በማማከር ስራ የሚሳተፉ ሴት አማካሪዎችን በልዩ ሁኔታ የሚበረታቱበት ስርዓት መዘርጋት  ያስፈልጋል።

በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ በምርምር ተቋማት የማማከር አገልግሎት ሙያዊ እና ሳይንሳዊ መፍትሄ ለማህበረሰቡ ማበርከት ይጠበቅባችዋል። የትምህርት ጥራት ሪፎርም አካል የሆነው የከፍተኛ ትምህርት ራስ ገዝነት ትግበራ ሂደት የሚያግዝ የማማከር አገልግሎት ገቢ አንዱ ምንጭ ሲሆን ተቋማት የውስጥ ገቢያቸውን በማሳደግ ወደ ራስ ገዝነት የሚያሻግራቸው የፋይናንስ ነጻነት እንዲያገኙ ያደርጋል። በተጨማሪም ኢንዱስትሪውን በማማከር ምርታማነታቸውን በማሳደግ ተኪ ምርቶችን ለሀገር ውስጥ በማቅረብ እና አለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ የመንግሥት የልማት ትኩረት አቅጣጫ ነው።

## 1. አላማ

በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪዎች መካከል ወጥ የሆነ የማማከር አገልግሎት ትግበራ እንዲኖር ለማድረግና የትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015 ለማስፈጸም ነው።

## 2. የባለድርሻ አካላት ድርሻ

የረቂቅ መመሪያው የዝግጅት ሂደት ላይ ከሁሉም የትስስር አካላት የባለሙያ ስብጥር ተዋቅሮ የተሰራ ሲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ማድረግ እና አስተያየት መቀበል ወሳኝ ምዕራፍ በመሆኑ ሁሉም የግልና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች፣ የተመረጡ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት፣ የተመረጡ

ኢንዱስትሪዎች እና ምርምር ተቋማት እንዲሁም የተመረጡ የቴክኖሎጂና ሰው ሀብት ልማት ዘርፍ ተቋማት ተሳትፈውበት ግብአት ተገኝቷል። በተጨማሪም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በተለያየ መድረክ መመሪያው ቀርቦ ተተችቷል ግብአት እና የማስተካካያ ሀሳቦች ተወስደው ማስተካካያ ተደርጓል። የእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በማማከር አገልግሎት ላይ የተሰጡትን የማስተካከያ ሃሳቦች እና እያንዳንዱ እርማት ከዚህ ሰነድ በአባሪ ተያይዟል።

## 3. የመመሪያው ይዘት

መመሪያው በአስራ ሁለት አንቀጾች የተዋቀረ ነው። የዚህ መመሪያ የተፈጻሚነት ወሰን በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ 1298/2015 በተጠቀሱ የትስስር አካላት ላይ ነው።

የመመሪያው ክፍል ሁለት በሁለት አንቀጾች የተዋቀረ ሲሆን የክፍሉ ዋና ሀሳብ የሚያጠነጥነው የማማከር አገልግሎት አደረጃጀት ላይ ነው። በትስስር አካላት መካከል ወጥ የሆነ አደረጃጀት እና የማማከር አገልግሎት ስራ የሚያስተባብር ክፍል ባለመኖሩ ምክንያት የማማከር አገልግሎት ስራው ወጥነት፣ ፍትሀዊነት እና ቅንጅታዊ አሰራር ላይ ውስንነት በመኖሩ በከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና እና የምርምር ተቋማት በተቋማቸው ውስጥ የማማከር አገልግሎት የሚያስተባብር ክፍል እንዲኖራቸው ይደነግጋል። ይህም በትስስር አካላት መካከል በማማከር አገልግሎት አመካኝነት የእውቀት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስራን በኃላፊነት እና በተጠያቂነት እንዲመራ ተደርጓል።

የመመሪያው ክፍል ሶስት ስለማማከር አገልግሎት መስፈርት ይደነግጋል። ይህም የማማከር አገልግሎት የሚሰጡ አማካሪዎች ግልጽ የሆነ የማማከር ዘርፍ፣ በቂ እውቀት፣ ሙያ፣ ክህሎት ባለመኖሩ እንዲሁም ከሚመለከተው አካል የተገኘ የማማከር አገልግሎት ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ባለመዘርጋቱ ፍትሃዊነትና ተጠያቂነት ለማስፈን የማማከር አገልግሎት ስራ ግልጽ የሆነ መስፈርት እንዲኖረው ተደርጓል።

የመመሪያው ክፍል አራት ስለ ማማከር አገልግሎት የተሳትፎ ፈቃድ አሰጣጥን ይደነግጋል። ይህም የተቋሙ ሰራተኞች ተቋሙ ከተቋቋመበት አላማ እና የስራ ጊዜ በሚሻማ መልኩ ከተቋሙ እውቅና እና ፈቃድ ውጭ የማማከር አገልግሎት ስራ የሚከናወኑ በመሆኑ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የማማከር አገልግሎት ስራ ተሳትፎ ፈቃድ መስፈርቱን ላሟሉ አካላት በተቋሙ የበላይ ኃላፊ ፈቃድ እንዲሰጥ ተደርጓል።

የመመሪያው ክፍል አምስት ስለ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል ይደነግጋል። በማማከር አገልግሎት ከሚገኝ ገቢ በማማከር ስራ የተሳተፈው ግለሰብ፣ ተቋም እና ሌሎች መካከል ፍትሃዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል የሚደነግግ ስርዓት ባለመኖሩ የተቋማቱን ገቢ ማሻሻል እንዲሁም አማካሪዎችን ማበረታታት

አልተቻለም። በመሆኑም በማማከር አገልግሎት ስራ ላይ የሚሳተፉ በከፍተኛ ትምህርት፣በቴክኒክና ሙያ ስልጠና እና በምርምር ተቋማት ሠራተኞች ለሚሰጡት የማማከር አገልግሎት ከሚገኝ ገቢ ድርሻ የማግኘት መብት ተደንግጓል። እንዲሁም በሴት አማካሪዎች ዋና መሪነት በተከናወነ የማማከር አገልግሎት ገቢ ክፍፍል የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንደማበረታቻነት ተቀምጧል።

የመመሪያው ክፍል ስድስት ስለ መመሪያውን የማስፈጸም ኃላፊነት፣ መመሪያውን ስለማሻሻል፣ መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ፣ የትስስር አካላት ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም እንደተቋማቸው ነባራዊ ሁኔታ የውስጥ መመሪያ እንዲያወጡ መብት እና ኃላፊነት ይሰጣል።

## 4. ህጉን ለማርቀቅ መነሻ የሆነ ፖሊሲ እና አዋጅ ስለመኖሩ

ረቂቅ መመሪያው ከአገሪቱ ህጎች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ከትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015፣ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ እና የሳይንስ፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ጋር መናበብ እንዲኖር እና ሌሎች ተዛማጅ የህግ ማእቀፎች ቅኝት ተደርጓል። በተጨማሪም የትስስር ስራ ተግዳሮት ለመለየት የተደረገ የዳሰሳ ጥናት እንደመነሻ ተወስዷል።